# መፈክሩ “**የታሰሩት የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ**” ነው መሆን ያለበት

ከ ነጻነት በቀለ

***ወያኔ*** በገንዘብ ብቻ ሳይሆን በእስረኛም ሃብታ ነው፡፡ ገንዘቡን እየቀማ እስረኛውንም በሃይሉ እያገተ ነው፡፡ ባብዛኛው የሚዘርፈውን ሃብት ለዋስትና ብሌ ካገር ውጭ ይሰደዋል ሌት ተቀን ባለማረፍ፡፡ ያገር አልበቃ ብሎት እስረኛውን ከውጭ ወደ አገር ይጠልፋል፡፡ ሃብታችንን ማሸሹ አዲስ እንዳልሆነ ሁሉ እስረኛም ጠልፎ ወደ አገር ማስገባቱ አሁን የተጀመረ ሳይሆን ገና በመንግስት መንበር ላይ መቀመጡን ሲጀምር ነበር፡፡ ከሱዳን ከጅቡቲ ከኬንያ ከኡጋንዳ ... ብርቅዬ የኢሕአፓ አባላትን የስደተኝነት መብታቸውን ገፎ ወደ አገር አስገብቶ ደብዛቸውን አጥፍቷል፡፡ ይህ የሆነው ከወር በፊት ሳይሆን ከብዙ አመታት በፊት ነበር የጀመረው፡፡ በዚህ ወቅት ውስጥ ከኢሕአፓ አባላት ሌሎችን ማለትም የኢድዩን የራሱን የወያኔ አባላት የነበሩትን የኦኤልፍ አባላትን . . . ሳይቀር አግቷል፡፡

***ያኔ*** የሰበአዊ መብት ተከራካሪ ነኝ ይሉ የነበሩ ግን የወያኔ አፍቅሮት ያወረው ድርጅት ቢጠየቅም ለኢሕአፓ አባላት መብት መጠበቅ ለመሟገት አልደፈረም፡፡ እንዲያውም ድርጅት ስላላቸው ድርጅታቸው ሊሟገትላቸው ይገባዋል ማለታቸው ምኝኛ የሰበአዊ መብት ምንንነት ያልተረዱ ግን ስሙን ለጥቅም የያዙ ስለመሆናቸው ራሳቸውን አጋልጠዋል፡፡ ለመርሳትም ቢሞከር ክርፋታቸው እስከ አሁን ይገማናል፡፡ ለነገሩ ያድርጅት ለማን እንደተከራከረ ወይም መዋቅርና አባላት ስለመኖሩ የጭለማ ድቅድቅ ነው፡፡ ለነገሩ ኑሮስ መቸ አለና?

**ይህን** እንደመንደርደሪያ ራሴን ካፍታታሁ ወደ ዋነኛው ትኩረቴ ላምራ፡፡ መቼም እርማት ለማቅረብ የሚታረመው ክፍል አምሮው ክፍት ሊሆን ይገባዋል፡፡ እርማት ማቅረቡ ማስኮረፉ ሲታወቅ ተቃውሞማ ማቅረብ ሊያስመታም ይችላል፡፡ ግን እንደሚባለው ድንጋይን ድንጋይ እንጅ ሙልሙል ዳቦ ማለቱ ለማንም አይጠቅምም፡፡ ተናጋሪውም አዳማጩም አይበላውምና፡፡ እና ዕውነቱን ይዘን ከመሸብን ቦታ ለማደር እንድፈር፡፡ የሰው ልጅ ፍትህ ሲያጣ አማራጩ ማመጽ ነው፡፡ በርግጥ “እሱ ያመጣውን እሱ እስኪመልሰው” የሚሉና ሃጢያት አውራጁ ፈጣሪ ነው ብለው “ማረና” የሚሉ አሉ፡፡ ግፍ ሰሪው ወያኔ ሆኖ ፈጣሪን ማማረር አይን ማጣት ነው፡፡ መታረም አለባቸው፡፡

***ወያኔ*** **የ**ሚያስረውንና የሚፈታውን ያውቃል፡፡ ሲያደርገውም እያረጀ ነው፡፡ ሲያስር ለማስፈራራት፣ ሲፈታ ደግሞ መሃሪ ለመባል ነው፡፡ ከለቀቃቸው አብዛኛዎቹ “ኮረንቲንና ፓለቲካን በሩቁ ነው” የሚል ትምህርት ቀስመው ይወጣሉ፡፡ አንዳንዱም ለነፃነት ለዲሞክራሲና ለፍትን መታገሉንና መታሰሩን ክዶ እንደተፈታ ሃይማኖተኛ ያውም ሰባኪ ሆኖ ይወጣል፡፡ አንዳንዱም ለድል የማያበቃ ግን አደናጋሪ ድርጅት ፈጥሮ ወያኔን ከመታግል ሃቀኛ የሆኑትን የሕዝብ ድርጅቶች የሚያክቸለችል ሆኖ ይወጣል፡፡ ባይበዙም በመታሰራቸው የተቀደሙ ይመስል ወደ ውጭ መጥተው ወደ ከፍተኛ ትምህርት መቅሰም የተሽጋገሩ አሉ፡፡ ዶክተር ተብለው አገር ለመምራት! ሁሉም ምልካም፡፡ ይሁንላቸው፡፡ መብታቸው ነውና፡፡ ችግሩ የሚጀምረው ሲያምሱን ነው፡፡ ያኔ ግን ከጅምሩ ብዙ ሳይፈላሰፉ ሊነገራቸው ይገባል፡፡

**መልካም፣** ወያኔ የፈለገውን ያስራል ይፈታል ብለናል፡፡ ዲያስፓራውም ለፈለገው ታሳሪ ብቻ ሲከራከር እያየን ነው፡፡ በየዕስር ቤቶቹ በሺዎች ታጉረው እያሉ “ እኔ እንዳርጋቸርው ነኝ” “አንዳርጋቸው ይፈታ” ለማለት እዚህም እዚያም ሰልፍ ይወጣል፡፡ ባንዳንድ አካባቢ ደግሞ አዳማጭም ተመልካችም በሌለበት ይወጣል፡፡ መሰረታዊ አላማው ፍጽም አልተስተካከለም፡፡ መፈክሩ መሆን ያለበት “ያለአግባብ የታሰሩ በሙሉ ይፈቱ” ነው፡፡ የሚናከስ ስራ ከሰራን ሺዎቹ ይፈታሉ፡፡ አንዳርጋቸው ከሺዎቹ ውስጥ ይሆናል፡፡ አንዳርጋቸውን ማስፈታት በሺህ የሚቆጠሩትን አያስፈታም፡፡ የሺዎቹ መፈታት በአንድ አንዳርጋቸው መፈታት ይተረጎማል ካልተባለ በስተቀር፡፡ ያም ይሁን ይህ ዛሬ በኢትዮጵያችን የታገቱን 40,000 በላይ እንደሆኑ ይነገራል፡፡ አንዳርጋቸው ቢፈታ 39,999 ምስኪን እስረኞች እዚያው በሰው በላው ወያኔ እየተሰቃዩ  የእስር ቤት ህይወታቸውን ይቀጥላሉ፡፡ የሚከብድ ስሌት አይመስለኝም፡፡ አንዳርጋቸው ጽጌ መጠለፍ የለበትም፡፡ የግለሰቡ መብት በየመንና በኢትዮጵያ አምባገነን ገዥዎች ተገፏል፡፡ ለማስፈታት ስንጮህ ግን መፈክሩ “እንዳርጋቸው ይፈታ” ሳይሆን **“ ሁሉም የፓለቲካ እስረኞች ይፈቱ”** መሆን አለበት፡፡መፈክሩ “ ያለአግባብ የታሰሩ ሁሉም ይፈቱ” ካልሆነ ለወያኔ የምንሰጠው ግንዛቤ “ ብቻ አንዳርጋቸውን  ፍታልን ስለሌሎቹ አያገባንም” ይሆናል”

እዚህ ላይ ከላይ ጠቀስ ያደረኩትን ጉዳይ ላብራራው፡፡ የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ድርጅት ግንቦት 7 ና ልሳናቸው ኢሳት ከተፈጠሩ ጀምረው በወያኔ ስለተጠለፉት የኢሕአፓ አባላት ላንዳፍታም አንስተው አያውቁም፡፡ ስለ ፋሺስቱ መንግስቱ ግን ካንዴም ሁለቴ አቅርበውት በሙቶ ሺዎች የፈጃቸውን ቢተሰቦች ክፉኛ አሳዝነውታል፡፡ “ አገሬ ኢትዮጵያ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ.. “ ማለት ይህ ነው፡፡ ሊቀመንበር ብርሃኑም ሆነ ዋና ጸሃፊው አንዳርጋቸው ጽጌ ለትግል ታሪካቸው ሬዙሜ ማጣፈጫ እንዲሆንላቸው ባንድ ወቅት ኢ ሕአፓ እንደነበሩና ላመራሩ እንደ ሹፌ በመሆን መስራታቸውን ይናገራሉ፡፡ ሹፌር በኢሕአፓ መዋቅር ውስጥ የት እንደሚመደብ ባይረዳኝም ነበርኩ ማለቱ ታሪክን ያሳምራልና መልካም፡፡ ሁለቱም ሰዎች ዛሬ ድርጅት ሰርተው እያሉ ለምን የድሮ ጓዶቻቸው የነበሩ የኢሕአፓ አባላት እንዲፈቱ ትንፍሽ አለማለታቸው ያሳዝናል፡፡ **ነግ በኔ ነው እንዴት አላሉም፡፡** እነ ዶክተር በወያኔ እስር ቤት ሲማቅቁ ኢሕአፓ እንዲፈቱ ሳያሰልስ ሞግቷል፡፡ እነሱ ድርጅታቸው ኢሕአፓ ይከራከርላቸው ያሉትም ድንቄም “የፍትህ ተሟጋች” ከርቸሌ የወረዱ ጊዜ ኢሕአፓ እንዲፈቱ የቻለውን ሁሉ ማድረጉ ያልቆየ ታሪክ ነው፡፡

በነገራችን ላይ ሰብ አዊ መብትን የሚጥስ አምባገነን መንግስት ብቻ ነው ብሎ ማጠቃለል ትክክል አይደለም፡፡ አንዳንድ በሚገባ ያልተገሩ ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ከአድሃሪ ገዥዎች ባላነሰ መልኩ መብትን እንደሚገፉ እያየነው አይደል? የበለጠ የሚያሳዝነው ደግሞ ዋሾ የሆኑ የመብት ተቆርቃሪ ድርጅቶች በየአገሩ ታይተዋል በኛም አገር ሳይቀር፡፡

ለወደፊት ያስተምረናል በማለት ይህን ድንቅ አባባል **ተውሼ** እንዳለ ከዚህ በታች አኒሬአለሁ፡-

***"First they came for the Socialists, and I did not speak out—
Because I was not a Socialist.
Then they came for the Trade Unionists, and I did not speak out—
Because I was not a Trade Unionist.
Then they came for the Jews, and I did not speak out—
Because I was not a Jew.
Then they came for me—and there was no one left to speak for me."***

መሬት ላይ ያለው ሃቅ እንደሚነግረን ወያኔ እስከሚጠፋ ድረሰ የማይጥሙትን የፓለቲካ ሰዎች ማሰሩን ይቀጥልበታል። አኛም " የፊቱን ባልሽን በምን ቀበርሽ? በሻሽ አዲሱ እንዳይሸሽ" ዓይነት በመሆን አዲሱ ታሳሪ አሮጌ እስቲሆን ማላዘናችን አይቀርም ማለት ነው የብልሕ ስራ ካልሰራን፡፡ ሰሞኑን አንዳርካቸው ነጻነቱን ተገፈፈ፡፡ እዚህም እዚያም ወጥተን "አንዳርካቸው ይፈታ" ስንል መክረማችን አይቀርም። አይበለውና ወራት ተቆጥረው ብርሃኑ ታገተ እንበል፡፡ አዲስ የነበረው አንዳርካቸው አሮጌ ይሆንና ላዲሱ እስረኛ " ብርሃኑ ይፈታ" አዙሪት ውስጥ በመግባት የተለመደውን ድራማ መስራት ይቀጠላል፡፡ አዲሱ እስረኛ ብርሃኑ ሳምንታት አስቆጥሮ ኢሳያስ ቢታሰር ብርሃኑ አሮጌ ሆኑ ጮሂ ከተገኘ ላዲሱ እስረኛ ለኢሳያስ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከእንዲህ አይነቱ  አዙሪት መውጣት የምንችለው መፈክራችን " **የታሰሩት የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ**" ሲሆን ብቻ ነው።

ለሕዝብ ነጻነት ሲታገሉ የታሰሩት በሙሉ ሰብ አዊ መብታቸው በወያኔ ተደፍሯል፡፡ ሁሉም የፓለቲካ እስረኛ ፍትህ ይፈልጋል፡፡ አበራሽ በርታ፣ ጸጋዬ ደብተራው፣ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ አንዱአለም ፣ርእዮት፣አብርሃም . . . . . .  ሁሉም ፍትህ ይሻሉ፡፡ ሁሉም የፓለቲካ እስረኛ አንዱ ካንዱ ሳይበልጥ ወይም ሳያንስ ወይም አንዱን ጀግራ ሌላው ተራ ተብሉ አድሎ ሳይጣልባቸው ለሁሉም እኩል ፍትህ ይገባቸዋል፡፡ ሕዝቡም ፍትህ ሲጠይቅ ላንዱ ብቻ ነጥሎ መሆን የለበትም፡፡ " **በግፍ የታሰሩት የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ**" ማለቱን መድፈር አለብን። ልዮነት ከፈጠርን ግን እኛም እንደወያኔ የፍትህ ጠላት ልንሆን ነው ማለት ነው፡፡ ለሁሉም ካልጮህን ነግ በኔ ሲሆን ማን ይጮህልኝ የሚለውን ከላይ የሰፈረ ዕውነታ ላለመርሳት እንሞክር፡፡

## ትናንትም ዛሬም ነገም መፈክራችን መሆን ያለበት " **የታሰሩት የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ**" ነው፡፡